ነፃ የሕግ ድጋፍ እና ተግዳሮቶች በፍትኃብሔር ጉዳዮች እና
የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት በኢትዮጵያ፡ ክፍተቶችና መፍትሔዎቻቸው

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ አዳራሽ

የካቲት 24/2009 ዓ.ም.

- **የአውደጥናቱ አጀንዳዎች/ርዕሰ -ጉዳዮች፡** 1. ነፃ የሕግ ድጋፍ እና ተግዳሮቶች በፍትኃብሔር ጉዳዮች እና
  2. የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት በኢትዮጵያ፡ ክፍተቶችና መፍትሔዎቻቸው የሚሉ ናቸው፡፡
- **ጽሑፍ አቅራቢዎች፡-** እንድ አጀንዳው ቅደምተከተል-
  1. አቶጌትነት ምትኩ (ሶሺዮ-ሌጋል ሪሰርቸር)
  2. አቶ አበራ ኃ/ማርያም (በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ዳይሬክተር)
- **አወያይ፡-**አቶ ታምራት ኪዳነማርያም /የማኅበሩ የቀድሞ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ/
- **ሐሳብ ሰጭ፡-** አቶ እንዳልካቸው ወርቁ (በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ የሕግ ማርቀቅና ማስረፅ ዳይሬክቶሬት ባለሙያ)
- **የአውደጥናቱ ቀን፡-** የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ከቀኑ 11፡30 ሠዓት
- **የአውደጥናቱ ቦታ፡-**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ አዳራሽ (ኤል ኤል ኤም)
- **በአውደጥናቱ ላይ የተገኙ ተሳታፊዎች፡-**የፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ ባለሙያዎች፣ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ክፍል መምህራኖችና የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ማዕከላት ተወካዮች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት መ/ቤት ተወካዮች፣ የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት ተወካዮች፣ የሙያ ማኅበራት ተወካዮች፣ የማኅበሩ አባላትና ሌሎችም

<u>አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር</u>



የማኅበሩ ፕሬዝዳንት የእንኳን ደህና መጣችሁ እና የመክፈቻ ንግግር በማድረግ የአውደጥናቱ በይፋ መከፈት ያበስሩት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ማህበሩ ከተለያዩ ባለድርሻ የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር እና ከአውሮፓ ሕብረት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የክልል ከተሞች ላይ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ መሆኑን እነዲሁም የተለያዩ የሕግ ጣናቶችን በማከናወን ሥነ-ሕግ እንዲያድግ የበኩሉን ኃላፊነት እየተወጣ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ፕሬዝዳንቱ የአውደጥናቱ ተሳታፊዎች በሚቀርቡት ጥናታዊ ፅሁፎች ላይ ሃሳብ አስተያየታችሁን በመስጠትና ተሞክሮዋችሁን፤ እውቀትና ልምዳችሁን ተካፍሉናላችሁ የሚል እምነት እንዳላቸው ለተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ በዕለቱ የተሰናዳው አውደጥናት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እንደሆነ፣ የፌደራል ጠ/ዐ/ሕግም አዳራሹን በነፃ በመስጠትና ሃሳብ ሰጭ በመመደብ የተባበረን በመሆኑ የላቀ ምስጋና ያቀረቡት የማኅበሩ ፕሬዝዳንት የዕለቱ ውይይት የተሳካ እንደሚሆን መልካም ምኞታቸውን ገልፀው የማኅበሩን ጥሪ አክብረው በአውደጥናቱ ላይ የተገኙ ባለሙያዎችን አመስግነዋል፡፡

<u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - አወያይ (የማኅበሩ የቀድሞ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>



አወያዩ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ካስተላለፉ በኋላ በእለቱ በተለያዩ ባለሙያዎች አማካኝነት 2 ጽሁፎች የሚቀርቡመሆኑን ጠቅሰው የመጀመሪያው ‹‹ነፃ የሕግ ድጋፍ እና ተግዳሮቶቹ በፍትኅብሔር ጉዳዮች›› በአቶ ጌትነት ምትኩ የሚቀርብ ሲሆን ቀጥሎም የማኅበራችን ተ/ዳይሬክተር በሆኑት በአቶ አበራ ኃ/ማርያም‹‹የተከላካይ ጠበቆች በኢትዮጵያ፡ ክፍተቶችና

መፍትሔዎቻቸው›› በሚል ርዕስ የሚቀርብ ዕሁፍ ይኖረናል ብለዋል፡፡ ባለሙያዎቹ የሚያቀርቡልን ዕሁፎችም በዋናነት ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን በሚመለከት በጥናት የተለዩ ተግዳሮቶች ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን፤ ቤቱም በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ አስተያየት የሚሰጥበት መድረክ እንደሚኖር፣ የቡድን ውይይት እና የወደፊት የመፍትሔ አቅጣጫዎች ላይ ምክክር የሚደረግ መሆኑን በመርሃግብሩ መሠረት ካስተዋወቁ በኋላ በዕሁፎቹ ላይ አስተያየት የሚሰጡት አቶ እንዳልካቸው ወርቁ በፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ የሕግ ማርቀቅና ማስረፅ ዳይሬክቶሬት ዐ/ሕግ ሲሆኑ የፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ እርሳቸውን በመመደብና አዳራሽ በመፍቀድ በመተባበሩ ያላቸውን የላቀ ምስጋና ያቀረቡት አቶ ታምራት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ክፍል ክሊኒካል ሌጋል ኢጁኬሽን ፕብሊክ ኢንተረስት ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ለአውደጥናቱ ስኬት የበኩሉን አስተዋፅዖ በማበርከቱ የተምህርት ክፍሉን አመስግነዋል፡፡ ወደ ጥናታዊ ዕሁፉ ከመግባታቸው በፊት የዕሁፍ አቅራቢዎችንና የሃሰብ ሰጪውን የሥራና የትምህርት ፕሮፋይል ያቀረቡ ሲሆን በቀረበው ፕሮፋይል መሠረት ጥናታዊ ዕሁፉን የሚያቀርቡልን ባለሙያዎች ጉዳዩ የሚመጥናቸው በመሆኑ አግባብነት እንዳላቸው ጠቅሰው ከቤቱ የሚነሱ ሃሳብ አስተያየቶች ዕሁፉን ለማዳበር አስፈላጊ እንደሆነ በመጠቆም በቀጥታ ጥናታዊ ዕሁፎቹ እንዲቀርቡ መድረኩን አስረክበዋል፡፡

<u>አቶ ጌትነት ምትኩ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>



የመጀመሪያውን ፅሁፍ ያቀረቡት አቶ ጌትነት ምትኩ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ተግዳሮቶች ላይ ጥናታዊ ፅሁፋቸውን የሚያቀርቡ መሆኑን እና በፍትኃብሔር ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ መሆኑን በመጥቀስ የጥናታዊ ፅሁፉ ወሰንን በመለየት የጀመሩ ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እ.አ.አ በ2013 ከባልደረባቸው ጋር በመሆን ስለ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ያጠኑት ጥናት እና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በአቶ አበራ ኃ/ማርያም በአራት የክልል ከተሞች የተጠና የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የፍላጎት ዳሰሳ መሠረት በማድረግ ገለፃቸውን የሚያቀርቡ መሆኑን ገልፀዋል።

የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ማለት በነፃ ወይም እጅግ አነስተኛ በሆነ ዋጋ የሕግ አገልግሎት የማቅረብ ተግባር እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ጌትነት የሕግ ድጋፍ አገልግሎት በውስጡ የሚይዛቸው ፍሬነገሮችን እንሚከተለው ዘርዝረዋቸዋል።

1. የሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነት የቃል ምክር አገልግሎት፣ የፅሁፍ ሥራዎች ማለትም ክስ፣ መልስ፣ የመልስ መልስ እንዲሁም ሌሎች የሕግ ማመልከቻዎችን፣ ደንበኛን ወክሎ የመቆምና የመከራከር፣ የማስማማት ወይም ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ማድረግ እና የመሳሰሉትን እንደሚያካትት ጠቁመዋል።
2. አገልግሎቱን የሚያቀርቡ አካላትን በሚመለከት የመንግሥት ተቋማት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት፣ ጠበቆች፣ የሕግ ባለሚያዎች፣ የሕግ መምህራንና በጎ ፈቃደኛ የሕግ ተማሪዎች፣ ፓራሌጋሎች ወዘተ እንደሆኑ ገልፀዋል።
3. የሕግ ድጋፍ አገልግሎቱ በፍትኃብሔር ችሎቶች፣ በወንጀል ችሎቶች፣ በአስተዳደር ፍ/ቤቶችና አካላት እንዲሁም በመሰል ተቋማት እንደሆነ ጠቁመዋል።

በፍትኃብሄር ጉዳዮች ላይ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን የሚሰጡ አካላትን ሲዘረዝሩ በቀድሞ የፍትህ ሚኒስቴር በአሁኑ ጠቅላይ ዐ/ሕግ እንዲሁም በሴቶች፣ሕፃናት እና ወጣቶች ሚኒስቴር እንዲሁም በተመሳሳይ የክልል ሴክተር መ/ቤቶች፤ የጥብቅና ፈቃድ ባላቸው ጠበቆች የሚሰጥ የ50 ሠዓት አስገዳጅ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት፤ በሙያ ማኅበራት (ለምሳሌ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር) እና መንግሥታዊ ባለሆኑ ድርጅቶች፤ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚገኙ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ማዕከላት እና የሕግ ትምህርት ክሊኒኮች፤ በጠቅላይ ፍ/ቤት የሕፃናት ፍትህ ፕሮጀክት እና የመሳሰሉት እንደሆኑ የጠቀሱት ፅሁፍ አቅራቢው አገልግሎቱን የሚያገኙ ሰዎችንም የለዩ ሲሆን የመጀመሪው ጠበቃ ቀጥረው ጉዳያቸውን ለመከታተል የሚያስችል የገንዘብ አቅም የሌላቸው የድሃው የሕብረተሰብ ክፍሎች እና በልዩ ሁኔታ ለተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮሚያዊና ፖለቲካዊ

ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ አካላት እንደሆነና ለአብነትም ሴቶች፣ ሕፃናት፣ ከኤች አይ ቪ ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች፣ የሕግ ተራሚዎች ወዘተ ዘርዝረዋል።

በነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡ ጉዳዮችን በተመለከተ ከወንጀል እና ከአስተዳደር ጉዳዮች ጋር ሲነፃጸር የፍትኃብሔር ጉዳዮች ቁጥር የሚበረክቱ መሆኑን አስታውሰው በተደጋጋሚ የሚቀርቡት ጉዳዮች የቤተሰብ፣ የቀለብ፣ የውርስ፣ የፍቺ፣ ንብረት ክፍፍል፣ አሳዳጊነትና ሞግዚትነት፣ የመሬት ድንበር ግጭቶች፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ወዘተ ናቸው ብለዋል። በነዚህ የፍትኃብሔር ጉዳዮች ላይ ከቃል ምክር አገልግሎት ጀምሮ እስከ ፍ/ቤት ቀርቦ በውክልና መከራከር ድረስ የሚዘልቁ የሕግ ድጋፍ አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል መሆኑን አክለዋል።

ከነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች ዘርፈ ብዙ መሆኑን እነዚህም በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ሊመደቡ እንደሚችሉ የገለፁት አቶ ጌትነት ውጫዊ እና ውስጣዊ ምክንያቶች (external and internal factors) እንደሆኑ ጠቁመው በእያንዳንዱ ምክንያት ስር ያሉትንነ ንዑሳን ተግዳሮቶችን በየፊርጁ ለይተዋል። እነዚህም፡-

1. **ውጫዊ ምክንያቶች** (external challenges)፡- በልዩ ሁኔታ ለችግሮች ተጋላጭ የሆነው ማህበረሰብ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳለው አለማወቁ፣ ይህ የሕብረተሰብ ክፍል በማኅበራዊ ግልጋሎቶች ውስጥ ያለው ሚና አናሳ እና ድምፁ የማይሰማ መሆኑ እና ወደ ሕግ በመሄድ ከሚገኘው ጥቅም ጉዳቱ የሚያመዝን አድርጎ የመረዳት እና መሳል ሁኔታ ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር የሚያያዝ ችግር እንደሆነ ገልጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የመብት ጥሰቶችን ችሎ የማለፍ ባህርይን የተላበሱ እንደሆኑ አብራርተዋል። በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚደርሱ በደሎች እንደ ነውር የማየትና ወደ ፍትህ አለማምጣት ችግር ሌላው ዋንኛ ምክንት እንደሆነምአቶ ጌትነት አስቀምጠዋል።

   ከላይ ከተጠቀሱት ማኅበራዊ ውጫዊ ምክንያቶች በተጨማሪ በበጎ አድራጎት ማኅበራት ላይ ተግባራዊ እየሆነ ያለው ሕግ (regulatory contect of CSOs) በራሱ ሌላኛው ውጫዊ ምክንያት እንደሆነ ያስቀመጡት አቶ ጌትነት በድጋሚ ምዝገባ ወቅት ብዙ የህግ ድጋፍ በመሰጠት መስክ ተሰማርተው የነበሩ ተቋማት ያልተመዘገቡና የተው መሆኑ፣ የሕግ ድጋፍ መርሃግብሮች መቀነስ እና ይህ ዓይነት አገልግሎትን የሚሰጡ መንግሰ,ሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማሽቆልቆል ችግሩን እንዳባባሰው ጠቁመዋል።

   የ70/30 እንዲሁም የ90/10 አቅጣጫዎች ተቋማቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ መፍጠራቸው የሚታወቅና ለአብነትም የሚጠቀሱ አካላት እንዳሉ ገልፀዋል።

ሌላው ከ50 ሠዓት የግዴታ የጥብቅና አገልግሎት ጋር በተያያዘ የቁጥጥር መላላት፣ በሁሉም አካባቢዎች በወጥነት አለመተግበሩ እንዲሁም የኃላፊነትና የተልዕኮ ግልፅነት ችግር ተጣቃሽ እንደሆኑ አስገንዝበዋል። በዩኒቨርሲቲዎች ያሉ ነፃ የሕግ ድጋፍ ማዕከላትም የጥብቅና ፈቃድ አሠጣጥ ውስንነት፣ የገንዘብ ውስንነት እና በሕግ ትምህርት ውስጥ የሚሰጥ ክሊኒካል ኤጁኬሽን ዓላማው በግልፅ አለመቀመጥ ተጨማሪ ምክንያቶች እንደሆኑ አብራርተዋል።

2. **ውስጣዊ ችግሮች** (Internal challenges)፡-ውስጣዊ ችግሮችን በሦስት ንዑስ ክፍሎች የተመለከተው ፅሁፍ አቅራቢው የመጀመሪያው ከተደራሽነት አንፃር የተቃኘ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከጥራት ፤የመጨረሻውና ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የቅንጅት ችግር እንደሆነ ካስቀመጡ በኋላ እንደየፈርጃቸው ተንትነዋቸዋል።

   ተደራሽነትን በተመለከተ አብዛኛው ነፃ የሕግ ድጋፍ ማዕከላት ከተሞችን ማዕከል ያደረጉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለገጠር ነዋሪው ተደራሽ አለመሆናቸውን፤ አገልግሎቱ ስለመኖሩ መረጃዎች ከማሰራጨት አንፃር ውስንነቶች መኖራቸውን እንዲሁም ፕሮግራሞቹ ሲቀረፁ የፍላጎት ዳሰሣ አለመከናወኑ ተጨማሪ ችግር እንደሆነ ገልፀው የገነዘብ ምንጮች ዘለቂታ ላይ አመኔታ አለመኖሩ እና የገንዘብ ድጋፍ ውስን መሆኑ አባባሽ ምክንያት እንደሆነ አቶ ጌትነት አስምረውበታል።

   ከአገልግሎት አሠጣጥ ጥራት ጋር የተያያዘው ችግር አንገብጋቢ መሆኑን የጠቆሙት ፅሁፍ አቅራቢው የተገልጋዮች የፍትህ ጥማትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊያሳካ የሚችል ባለሙያ መቅጠር፣ ተከታታይ ሥልጠና የመስጠት፣ የሙያ ሥነምግባር ደንቦች፣ ሞዴል ሕጎች ማውጣት ወዘተ ላይ ችግር መኖሩን በማብራራት ገለፃቸውን ያጠናቀቁ ሲሆን ባቀረቡት ፅሁፍ ላይ ሃሳብ፣ አስተያየት እና ጥያቄዎችን ቤቱ ሊያቀርብ የሚችል መሆኑን ጠቅሰው መድረኩን ለአወያዩ አስረክበዋል።

<u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - አወያይ (የማኅበሩ የቀድሞ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>

አወያዩ አቶ ታምራት መድረኩን ተረክበው አቶ ጌትነት ምትኩን በማኅበሩ እና በራሳቸው ስም አመስግነው በተያዘው ጊዜ ውስጥ ሰፋፊ ጉዳዮችን በተለይም በፍትኃብሔር ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ከነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ጋር የተያያዙ ነጥቦችን መዳሰሳቸውን ከትርጓሜው ጀምሮ በሀገራችን ያለውን ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን በመለት ማብራራታቸውን

፤በማጠቃለያ መልክ አቅርበው በድጋሚ አቶ ጌትነት ካመሰገኗቸው በኋላ የሚቀጥለውን ጥናታዊ ፅሁፍ እንዲያቀርቡ ለአቶ አበራ ኃ/ማርያም መድረኩን አስተላልፈዋል፡፡

<u>አቶ አበራ ኃ/ማርያም- ፅሁፍ አቅራቢ (የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ተ/ዳይሬክተር)</u>



“የተከላካይ ጠበቆች በኢትዮጵያ፡ ክፍተቶችና መፍትሔዎቻቸው” በሚል ርዕስ ያጠኑትን ጥናት መሠረት ያደረገ ፅሁፍ የሚያቀርቡ መሆኑን ጠቅሰው በቀጥታ ወደ ገለፃ ከመግባታቸው በፊት የሚያቀርቡትን ጥናት ይዘት በሚመለከት በቅደምተከተል ዘርዝረዋል፡፡ በዚህም መሰረት የፅሁፉ ማግቢያ እንደሚኖረው፣ ተከላካይ ጠበቃን በሚመለከት የተለያዩ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚቀርብ፣ የተከላከይ ጠበቆች ተቋምን በሚመለከት የኢትዮጵያ የሕግና የፖ/ሊሲ መዋቅር ምን እንደሚመስል የሚዳሰስ ክፍል መኖሩን፣ በአገልግሎቱ ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶች፣ የአገልግሎቱ ተደራሽነት ና የተቋሙ አፈፃፀም፣ የአገልግሎቱ ብቁ መሆን አለመሆን እና ጥራቱ እንዲሁም ማጠቃለያ እንደሚኖረው በማበራቸው ላይ ዘርዝረዋል፡፡

በተለያዩ ሀገራት ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት በተለያየ አግባብ የሚሰጥ መሆኑን የጠቆሙት ፅሁፍ አቅራቢው pro bono የሚባለው የአገልግሎት ዓይነት በጠበቆች የሚሰጥ ሲሆን በተለያየ መልኩ

ጉዳዮች ለጠበቆች የሚመደብላቸው መሆኑን፤ judicare ወይመ contracting model የሚባለው አገልግሎት በግል ጠበቆች የሚሰጥ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ለችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ እና ጠበቃ የመቅጠር አቅም ለሌላቸው ሰዎች መንግሥት ውልን መሠረት በማድረግ ክፍያውን ለጠበቆቹ የሚፈፅምበት አሰራር መሆኑን፤ community legal services የሚባለው ደግሞ በጠበቆች ማኅበር ወይም ሌላ ተመሳሳይ በህርይ ባለው ማኅበር አማካኝነት የሚቀርብ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት መሆኑን እንዲሁም በተከላካይ ጠበቆች አማካኝነት በመንግሥት የሚሰጠው ሌላው ዓይነት የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት መሆኑን በዝርዝር አብራርተዋል።

በወንጀል ክስ የቀረበባቸው ሰዎች በጠበቃ የመወከል መብት ሊኖራቸው እንደሚገባ የካሊፎርኒያ ዜግነት ያላት ክላራ የተባለች የመጀመሪያዋየሴት ጠበቃ በ1893 ያደረገችው ንግግር እንደማዕዘን ድንጋይ የሚታይ መሆኑን ፤በኋላም በአሜሪካ ሕገመንግሥት 6ኛ አሜንድመንት ላይ ይህ መብት እንዲካተት መደረጉን፤ የአሜሪካን ጠቅላይ ፍ/ቤትም *Gideon v. Wainwright*ኬዝ ላይ መንግሥት በወንጀል ለተከሰሱ ሰዎች ተከላካይ ጠበቃ ሊያቆምላቸው እንደሚገባ የወሰነበትን አግባብ የጠቀሱት አቶ አበራ እ.አ.አ. ለመጀመሪያ ጊዜ ኒው ጀርሲ ውስጥ የተቀናጀ የተከላካይ ጠበቆች ቢሮ ተመሥርቷል ብለዋል። አያይዘውም በብራዚል፣ ኮሎምቢያ፣ ኒካራጓ፣ ሜክሲኮ፣ ሆንዱራስ፣ ፓናማ፣ ፓራጓይ፣ ቬንዙዌላ እና ፔሩ የተከላካይ ጠበቆች ተቋምን በሕገ-መንግሥቶቻቸው ያቋቋሙ መሆናቸውን፤ አርጀንቲና፣ ቦሊቪያ፣ ቺሊ፣ ኢኳዶር እና ሌሎች ሀገራትም በሕጎቻቸው የተከላካይ ጠበቆች ተቋማትን ማቋቋማቸውን የገለጹት ጽሑፍ አቅራቢው የብራዚልን ሕገ-መንግሥት በመጥቀስ ጠበቃ ለመቅጠር አቅም ለሌላቸውና የወንጀል ክስ ለቀረበባቸው ሰዎች መንግሥት የጥብቅና አገልግሎትን በነፃ ሊያቀርብላቸው እንደሚገባ የሚያስቀምጥ መሆኑን አክለው ገልፀዋል። በ በራዚል የተከላካይ ጠበቆች ተቋም የሚያቋቁመው እና የሚያደራጅ እራሱን የቻለ ሕግ የወጣ መሆኑንና ይህ ሕግ ተሻሽሎ ነፃና እራሱን የቻለ በራሱ በጀት የሚተዳደር ተቋም መመስረቱን አመልክተዋል። የተከላካይ ጠበቆች ተቋምን በሕገመንግሥቱ መቋቋም የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ወገኖች ፍትህ የማግኘት መብት ዋስትና ነው ሲሉ ተደምጠዋል። ከብራዚል ተሞክሮ በተጨማሪ የደቡብ አፍሪቃን የሕግ ማዕቀፍ የዳሰሱ ሲሆን በደ/አፍሪቃ የተከላካይ ጠበቆች ቢሮ እራሱን በቻለ ሁኔታ የተዋቀረ እና legal aid board በሚባል አካል የሚመራ መሆኑን ፤የ ቦርዱ ሊቀመንበሩም የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ እንደሆነ አውስተው ተቋሙ በቀጥታ በፓርላማው በጀት የሚመደብለት መሆኑን እና በፍትህ ሚኒስቴር በኩል ሪፖርት የሚያቀርብ መሆኑን ጭምር አብራርተዋል።

የጥናቱ ኣላማዎች የኢትዮጵንያን የሕግ ሥርዓት እና የፖ/ሊሲ ማዕቀፍን ለመዳሰስ፤ የተከላካይ ጠበቆች ቢሮ ተቋማዊ መዋቅር፣ ተደራሽነታቸውንና አፈፃጸማቸውን ለመገምገም እና የሚሰጡት አገልግሎት ብቃትና ጥራት ለመመርመር እንደሆነ የጠቀሱት ፅሁፍ አቅራቢው የተከላካይ ጠበቆች በሀገራችን በ1988 በፌደራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የተዋቀረ መሆኑን እና ሌላ የሕግ መሠረት እንደሌለው ገልፀዋል፡፡ የተከላከይ ጠበቀች በሮ በፌደራለ ደረጃ የተዋቀረው የደረግ ባለስለጣናት በዘር ማጥፋት ወነጀል በተከሰሱበት እ.ኤ.አ. በ1994 መሆኑን ፤ የጀመረውም በጥቂት ጠበቆች አማካይነት መሆኑን ፤በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ የጠበቆቹም ቁጥር ከአራት እና አምስት ወደ ሰላሳ ከፍ ማለቱን አውስተዋል፡፡

የዓለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን በአንቀፅ 14 (3)(መ) ስር እንደተመለከተው አንድ የተከሰሰ ሰው በራሱ ጠበቃ የመቅጠር አቅም ከሌላውና ትክክለኛ ፍትህን ለማስገኘት ጠበቃ ማቀም የሚያስፈልግ ከሆነ በመንግሰት ወጭ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ሊሠጥ የሚገባ መሆኑን ጠቅሰውዓለምአቀፉ የሕፃናት መብቶች ቃልኪዳን እና የአለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ድንጋጌዎች መቀመጣቸውን አብራርተዋል፡፡ አቶ አበራ ከዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች ባሻገር የሀገራችን ሕጎችን የዳሰሱ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገመንግሥት የተከሰሱ ሰዎች በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትህ ለጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው በሚል በአንቀፅ 20 (5) ስር ማስፈሩን ፤ የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀፅ 16 (2) (በ) የተከላካይ ጠበቆችን ቢሮ ማደራጀት የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት ተግባር እና ኃላፊነት እንደሆነ መመልከቱን ጠቅሰዋል፡፡

የፌደራል ፍ/ቤት ጠበቆች የአስተዳደር ደንብ በአንቀፅ 49 ስር እንደተመለከተው ጠበቆች 50 ሠዓት ነፃ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን የሚደነግግ መሆኑን፤ የወንጀል ፍትህ ፖ/ሊሲው የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ለተከሰሱ ሰዎች ፈጣን፣ ተደራሽና ፍትሃዊ መሆን እንዳለበት በግልፅ የሚያስቀምጥ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አበራ፤ አንድ የተከሰሰ ሰው ወንጀሉን በአግባቡ ሊከላከል በሚችልበት አግባብ በጠበቃ መወከሉን በመርማሪ አካላት፣ በዐቃቢያነ ሕግ እና በፍ/ቤቶች መረጋገጥ እንዳለበት ፖ/ሊሲው ያስቀምጣል በማለት አክለዋል፡፡ ቀደም ብለው ሕገመንግሥቱን በመጥቀስ የገለፁትን በማስተዋስ የተከሰሱ ሰዎች በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትህ ለጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳላቸው በፖ/ሊሲው በገልጽ መስፈሩን አልፎ ተርፎም

በሰብዓዊ መብት ጥሰት ወይም በከባድ ወንጀል ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን ጠበቃ የመቅጠር አቅም ለሌላቸው ሰዎች የፍትኃብሔር ጉዳይ ማለትም ካሳን የሚመለከቱ ጉዳዮች በመንግሥት ወጭ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚገባ የወነጀል ህግ ፖሊሲው ማስቀመጡን ገልፀዋል፡፡ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በበቂ ሁኔታ አገልግሎቱን የሚሰጥ ነፃና ገለልተኛ የተከላካይ ጠበቆች ተቋም መቋቋም እንዳለበት በፖሊሲው ውስጥ መስፈሩን አቶ አበራ ጠቁመዋል፡፡



እ.አ.አ. ከ2013 እስከ 2015 የሚሸፍነው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች አክሽን ፕላን እንዳስቀመጠው በክልል እና በፌደራል የተከላካይ ጠበቆች ቁጥርን ለማሳዳግ ጥረት የሚደረግ መሆኑን፤ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶችም እንደወንጀሎች ክብደት ተከላካይ ጠበቃ የሚመደብበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚገባ፤ እንዲሁም የተከላካይ ጠበቆችን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ተከታታይ ስልጠና ሊሰጥ እንደሚገባ የተቀመጠ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ያቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ የዘጠኙም ክልሎች የተከላካይ ጠበቆች ተወካዮች፣ የፖሊስ እና የማረሚያ ቤት ተወካዮች፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ተወካዮች፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወካዮች፣ የፍትህ ሚኒስቴር፣ ፌደራል ፖሊስ እና የፌደራል ማረሚያ ቤት ተወካዮች እንዲሁም የሕግና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ተወካዮች መረጃዎችን በማሰባሰብ ረገድ ተሳታፊ የሆኑበት መሆኑን፤ በተሌዩ ማረሚያ ቤቶች በመዘዋወር በተለያዩ ስልቶች መረጃዎች የተሰባሰቡ መሆኑን፤ በመጨረሻም የጥናቱ ግብዓቶችን በመተንተን በተከላካይ ጠበቆች የሚሰጥ የሕግ ድጋፍን የሚመለከቱ ክፍተቶች መለየታቸውን ገልፀዋል፡፡

ሀገራችን ያፀደቀቻቸው ዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ቃልኪዳኖች፣ ሕገመንግሥቱ እና ሌሎች ሕጎች በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በራሳቸው ጠበቃ መቅጠር ለማይችሉ የወንጀል ተከሳሾች የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎት ሊሰጣቸው እንደሚገባ የሚያስቀምጡ መሆኑን የጠቀሱት ፅሁፍ አቅራቢው እነዚህ ሕጎች ብቻቸውን በቂ አለመሆናቸውን ጠቁመው በሕገመንግሥቱ የተቀመጠውን የተከሰሱ ሰዎች መብት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችልና ነፃና ገለልተኛ የሆነ የተከላካይ ጠበቆች ቢሮን የሚያቋቁም የተሟላ የሕግ ሥርዓት አለመኖሩን በአፅንዕዖበመግለጽ የተከላካይ ጠበቆች ቢሮ ያልተቋቋመበት ክልል መኖሩን እና የተቋቋመባቸው አከባቢዎችም ቢሆኑ የተሟላ የሰው ኃይል የሌላቸው እና የፋይናንስ ችግሮች ያሉባቸው እንደሆኑ አስታውቀዋል፡፡ የአስተዳደር እና የሥራ ነፃነት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ግልፅ የሆነ ተቋማዊ መዋቅር አለመኖሩ፣ ተወዳዳሪ የሆነ የደመወዝ፣ የጥቅማጥቅምና የእድገት መዋቅር ያልተዘረጋ መሆኑና መሰል ችግሮች ሠራተኞቹ በሥራው ላይ እንዳይቆዩ እና ሌሎች ጠንካራ የሕግ ባለሙያዎችም ቢሮውን ከመቀላቀል እንዲቆጠቡ ምክንያት መሆናቸውን ፅሁፍ አቅራቢው አስቀምጠዋል፡፡

የተከላካይ ጠበቆች ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን ለማግኘት የሚያስችል ወጥ የሆነ መስፈርት አለመኖሩ ሌላኛው ችግር መሆኑንየገለጹት ፅሁፍ አቅራቢው በተግባር ላይ ያለው ልምድ የሚያመለክተው የአገልግሎቱ ተጠቃሚወችን ለመለየት የሚገለገሉበት መስፈርት የወንጀሉ ክብደትና ጠበቃ ለመቅጠር የሚያስችል አቅም አለመኖር መሆኑን አውስተው በከባድ ወንጀል ተከሰው ያለተከላካይ ጠበቃ ጥፋተኛ ተብለው ማረሚያ ቤት የወረዱ አያሌ ታራሚዎች መኖራቸውን የጥናታቸው ግኝቶችእንደሚያመለክቱ ጠቅሰዋል፡፡ በብዙ ክልሎች ይህን አገልግሎት የሚሰጡ ቢሮዎች ከፍተኛ የሰው ኃይል እጥረት ያለባቸው፣ የበጀት ውስንነትና ሥራውን ለማስኬድ የሚያስችሉ የተሟላ የቁሳቁስ የሌላቸው መሆኑን አክለው ገልፀዋል፡፡ ተቋሙ የሚገባውን አትኩሮት ያላገኘ መሆኑን እና በአግባቡ ያልተዋቀረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዛት ያላቸው የጥናቱ ተሳታፊወች ግምገማ አገልግሎት አጥጋቢ እንዳልሆነ መግለፃቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡

የአገልግሎቱ ጥራት እና አቅርቦት ላይ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዳሉት የጠቆሙት ፀሃፊው አገልግሎቱ በአብዛኛው ከስር ፍ/ቤቶች ሳይሆን ከከፍተኛ ፍ/ቤቶች የሚጀምር መሆኑ፤ ከተከላካይ ጠበቆች ቁጥር አንፃር ያለው የጉዳይ ብዛት ሲገመገም እጅግ በጣም የማይመጣጠን በመሆኑ በአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሰደረ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት ጠበቆች ተገቢውን ዝግጅት አለማድረግና በቀነ-ቀጠሮ በችሎት አለመገኘትና መሠል የጥራት ችግር መንስዔዎች የሚስተዋሉ መሆናቸውን በማብራራት ገለፃቸውን አጠናቀዋል፡፡

<u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - አወያይ (የማኅበሩ የቀድሞ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ)</u>

አወያዩ አቶ ታምራት በአቶ አበራ ኃ/ማርያም የቀረበውን የተከላካይ ጠበቆች ነፃ የህግ ድጋፍን በሚመለከት የተለያዩ ሀገራት በዘርፉ ያላቸውን ተሞክሮ፣ በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች በጠበቃ ተወክለው ጉዳያቸውን የመከታተል መብት ከዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቃልኪዳን ስምምነት፣ ከሕገመንግሥቱ እና ሌሎች የሀገራችን ሕጎች አንጻር ከተነተኑ በኋላ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ባካተተና ተሳታፊ ባደረገ ጥናት በተከላካይ ጠበቆች ቢሮ የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን እና የሕግ ማዕቀፉ ያሉ ክፍተቶች በተለይም እራሱን የቻለ ሕግ እና ተቋማ አለመኖሩ ችግሩን የባባሰ መሆኑን፤ እንዲሁም ለአገልግሎት ሰጭ ጠበቆቹ የደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም እና የእድገት መዋቅር አለመኖሩ፣ ተከታታይ ሥልጠናዎች አለመኖራቸው፣ የጠበቆች ቁጥር እና ጥራት ውስንነት መኖሩን እና ሌሎች መሠረታዊ ችግሮችን አንስተው አሁን ባለው ሁኔታ የአገልግሎቱ ጥራት እና ተደራሽነት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ የፈጠረ መሆኑን በስፋት እንዳብራሩ አሰተውሰው ሁለቱንም ፅሁፍ አቅራቢዎች ካመሰገኑ በኋላ በቀጥታ ወደ ቤቱ ሃሳብ፣ አስተያየትና ጥያቄ እንደሚያልፉቀጥለውም በተዘጋጁ የመነሻ ጥያቄዎች ላይ የቡድን ውይይት እንደሚኖር ገልፀው መድረኩን ለተሳታፊ ታዳሚው ክፍት አድርገዋል።

<u>አቶ መዓዛ ኃይማኖት - ከፌደራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ</u>

ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትን በሚመለከት የሕግ ማዕቀፍ የለንም በሚለው እንደማይስማሙ ፤ ሕገመንግሥቱን ጨምሮ በጠበቆች ሥነምግባር ደንብ እንዲሁም በወንጀል ፍትህ ፖሊሲው ላይ የተቀመጡ አንድ አንድ አቅጣጫዎች መኖራቸውን ፤ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ስትራቴጂም በረቂቅ ደረጃ ያለ መሆኑን ጠቅሰው እነዚህ ያሉንን ነገሮች ይዘን በሌሉን ሕጎች ላይ ትኩረት መስጠት የተሸለ መሆኑን ጠቁመዋል፡፤ አያይዝወም በአገልግሎቱ ዙሪያ የጥራት ችግር መኖሩን በመግለፅ ይህን ጉዳይ በባለቤትነት የሚሰራ አካል በጠቅላይ ዐ/ሕግ መኖሩን በማከል አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

<u>አቶ እዮብ ካሞ - ከኦሮሚያ ሴቶችና ሕፃናት ቢሮ</u>

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ይህን አውደጥናት በማዘጋጀቱ አመስግነው ይሄ ማኅበር ከነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በተግባር ምን እየሰራ ነው በማለት ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡

<u>አቶ ፈቃዱ ደምሴ - ከፌደራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ</u>

በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 37 ስር የተቀመጠውን መብት መሬት አውርዶ ከማስተገበር አንፃር የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ሊመሰገን እንደሚገባ ጠቅሰው ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን በተመለከተ የተለያዩ ሀገራት ተሞክሮን በዝርዝር ካብራሩ በኋላ የሀገራችን ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ቡራቡሬ ነው በማለት አስተያየት ሰጠድተዋል፡፡

<u>ሶፍኒት መኮንን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ክፍል</u>

ክሊኒካል የሕግ ትምህርት ዋናው ዓላማ አካዳሚክ ወይም ትምህርታዊ መሆኑን፤ ትምህርታዊ ዓላማውን በማሳካት እግረመንግድ ለአገልግሎት ፈላጊው የህግ ድጋፍ የሚሰጥ ስረአት መሆኑን ገልፀው ከአዲስ አበባ በክልል ያለው እንቅስቃሴ የሚሻል መሆኑን በተለይም ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ከማግኘት አንፃር በክልሎች የተሻለ መሆኑንጠቁመዋል፡፡ጠቅላይ ዐ/ሕግም የነፃ የሕግ ድጋፍ ላይ በስፋት መስራት እንዳለበት በማሳሰብ የበጎ አድራጎት ማኅበራት አሁን ባላቸው ውስን ኃብት በመንግሥት ባለድርሻ አካላት ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር አዳጋች ቢሆንም ሊታሰብበት እንደሚችል አስቀምጠዋል፡፡

<u>አቶ ስሜነህ ተክሉ - አድቮኬትስ ኢትዮጵያ</u>

የነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ፍላጎት ብዙ መሆኑን ፤ የተናጠል ሥራ ውጤታማና አዋጭ መሆን እንደማይችል ጠቅሰው ለወደፊት ቀጣይና ተከታታይ የምክክር መድረክ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

<u>አቶ ሙሉቀን ይታይህ - ከደ/ብርሃን ዩኒቨርሲቲ</u>

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሦስት መሠረታዊ ዓላማዎች ያሏቸው መሆኑን ጠቅሰው የመጀመሪያው የመማር ማስተማር ሥራ ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ተልዕኮ እና የምርምር ሥራ እንደሆኑ ፤ነፃ የሕግ ድጋፍ በፍትኃብሔር ጉዳይ ላይ የሚያተኩር መሆኑን ፤ ‹‹ነፃ የሕግ ድጋፍ››

ከሚባል ‹‹ነፃ የሕግ አገልግሎት›› ቢባል የተሻለ እንደሆነ አውስተው የጠቅላይ ዐ/ሕግ መ/ቤት በዚህ ዘርፍ ትልቅ ሥራ መስራት አለበት ብለዋል፡፡

<u>አቶ ዘመኑ የስጋት - ከድሬ ደዋ ዩኒቨርሲቲ</u>

ጠቅላይ ዐ/ሕግ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን የወንጀል ጉዳዮች ላይ በሚሰጡ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ላይ የጥቅም ግጭት አይፈጥርበትም ወይ?የሚል ጥያቄ አንስተው ወደ አስተያየታቸው ያለፉ ሲሆን ከደ/ብርሃን የመጡ ተሳታፊን ሓሰብ በመጋራት ዩኒቨርሲቲዎች 3 ዋና ዋና ዓላማዎች እንዳሏቸውና ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ደግሞ የሕግ ትምህርት ቤቶች አንዱ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸው እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

<u>አቶ ጌትነት ምትኩ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

ሕገመንግሥቱ በአንቀፅ 37 ስር ፍትህ የማግኘት መብትን ያስቀመጠ ሲሆን የዚህን መብት መከበር ለማረጋገጥ comprehensive legal aid system የሚያስፈልግ በመሆኑን ይህን ዓይነት ሥርዓት እንዴት ማምጣት እንችላለን የሚለው ዋነኛው ነጥብ እንደሆነ ጠቅሰው በጥናታችን ላይ የሀገራት ተሞክሮን ለማስቀመጥ ጥረት መደረጉን በፍትኃብሔርም ሆነ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ውስጥ እስራኤልና አውስትራሊያ መልካም ተሞክሮ የላቸው ሃገራት መሆናቸው ጠቅሰዋል፡፡ የሙያ ማኅበራትን በተመለከተ ሕጉ የሚጥላቸው ተግዳሮቶችን እንደ መሠረታዊ ችግር አውስተዋል፡፡

<u>አቶ ፈቃዱ ደምሴ - ከጠቅላይ ዐ/ሕግ</u>

ጠቅላይ ዐ/ሕግ ጠበቆችን እንዲያስተዳድር የሕግ mandate ያለው መሆኑን ገልፀው በጥብቅና አስተዳደር መሠረት ሦስት ዓይነት የጥብቅና ፈቃድ መኖራቸውን እነዚህም የመጀመሪያ፤ በማናቸውም እና ልዩ የጥብቅና ፈቃድ መሆናቸውን ከዘረዘሩ በኋላ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ የሚሰጣቸው አካላት በነፃ በበጎ አድራጎት ሥራ የጥብቅና አገልግሎቱን ለሚሰጡ ሰዎች መሆኑን ሆኖም በሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው ሰዎች ይህን ፈቃድ የመሰጠት ለፈቃድ ሠጭው አካል አለመሰጠቱን ገልጸዋል፡፡ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ስትራቴጂ በረቂቅ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ፈቃዱ በሂደት ተግባራዊ የሚሆን እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

አቶ እንዳልካቸው ወርቁ- ሃሳብ ሰጭ



ዜጎች ፍትህ የማግኘት ሕገመንግስታዊ መብት እንዳላቸው ሕገመንግሥቱ የሚያስቀምጥ መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ለዚህ መብት መረጋገጥ የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ መሆናቸው እሙን እንደሆነ አመልክተዋል። ከየትኛውም የመንግሥት ተቋማት በላቀ ሁኔታ ጠቅላይ ዐ/ሕግ የዚህን መብት በማስከበር ረገድ የህግ ግዴታ ያለበት መሆኑን ያመለከቱት ሃሳብ ሰጭው በተለያየ አደረጃጀት ውስጥ የዚህን መብት የማረጋገጥ ሥራ የሚሠራ መሆኑን ጠቅሰው የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትና የጥብቅና አስተዳደር በዋናነት የሚመለከተው አካል እንደሆነ ጠቁመዋል። አያይዘውም ከዚህ ተቋም ባሻጋር የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር እና ሌሎች መንግሥታዊ ያለሆኑ ተቋማት ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትን በፌደራልም ሆነ በክልሎች ማዕከላትን በማቋቋም ጭምር ዓይነተኛ ሚና እየተጫወቱ ቢሆንም ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት በተቀናጀ መልኩ፣ ጥራትና ደረጃውን ጠብቆ ይሰጣል ለማለት የማያስደፍር እንደሆነ ሁላችንም የምንረዳው ነው ብለዋል። የተቀናጀ አገልግሎት እንዲኖር የተቀናጀ የሕግ መዋቅር የሌለን ሲሆን ጠቅላይ ዐ/ሕግ ውስጥ የሚገኘው የፍትኃብሔር ክርክር ጉዳዮች፣ የጥብቅና አስተዳደሩ፣ በጠቅላይ ፍ/ቤት ስር የሚገኘውም የተከላካይ ጠበቆች ፅ/ቤት፣ እንዲሁም ሌሎች ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን የሚሰጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት በተናጠል የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው እንዲሁም የተጠቃለለ የሕግ ማእቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት አገልግሎቱ የተቀናጀ እንዳይሆን ምክንያት እንደሆነ አብራርተዋል።

<u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - አወያይ</u>

የቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ፅሁፍ አቅራቢዎቹም ሆነ ሃሳብ ሰጭው አስተያየታቸውን የሰጡ በመሆኑቸው አመስግነው በቀጥታ ተሳታፊው በቡድን ተደራጅቶ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ለየቡድኑ እንዲከፋፈል በማድረግ አምስት ቡድኖች እንደሚዋቀሩ፤ በየቡድኑ ውይይት ተደርጎ እያንዳንዱ ቡድን በሚወከለው ስዉ አማካኝነት የቡድኑን የውይይት ጭማቂ እንደሚያቀርብ ና ተሳታፊውም አጠቀላይ ውይይት እንደሚካሄድ ለተሳተፊወች ጠቁመዋል። በዘህም መስረት 5 ቡድኖች ተመስርተው ውይይት አካሂደዋል። የውይይቱ ውጤት ከዚህ እነደሚከተለው ቀረቧል፦

<u>ቡድን 1 - የአገልግሎቱ ወሰንን በሚመለከት (አቶ ዘመኑ የስጋት - ከድሬ ደዋ ዩኒቨርሲቲ (የቡድን 1 ተወካይ የቡድን ውይይቱን አቅራቢ))</u>





ሁሉም የአገልግሎት ዓይነት መሰጠት እንዳለበት ጠቁመው የፍትኃብሔር፣ የወንጀል እንዲሁም በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ጭምር ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት አድማስ መስፋት እንዳለበት አስረድተዋል። በወንጀል ነክ ጉዳዮች ላይ የተከላካይ ጠበቆች ቢሮን በሚፈለገው ልክ ማጠናከር ተገቢ እንደሆነ ያስቀመጡት የቡድኑ አባላት ከአንዱ አገልግሎት ሰጭ ወደ ሌላው የማስተላለፍ ሥርዓት (referral system) ቢኖር መልካም እንደሆነና አገልግሎት ሰጭዎቹ ጥርት ባለ መልኩ ስፔሻላይዝ አድርገው ወሰናቸውን ቢያውቁ ጥሩ እንደሆነ አስቀምጠዋል።

የባለድርሻ አካላትን ኔትዎርክ ማጠናከር ሌላው መፍትሄ እንደሆነ አስረድተው የሚመለከተው የመንግሥት አካልም ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የህግና የፖሊሲ እንዲሁም የተቋም መዋቅር ሊያዘጋጅለት እንደሚገባ አመልክተዋል። ተቀዳሚው መፍትሔም ብሔራዊ የሆነ መዋቅር

በመዘርጋት የተለያዩ የገንዘብ ማመንጫ አጋጣሚዎችን መጠቀም ለምሳሌ victim fund መጠቀም እንደሚቻል አስረድተዋል፡፡

የቀረበው ገለፃ ላይ ጥያቄና አስተያየት

<u>ሶፍኒት መኮንን - ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ</u>

የተደፈሩ ሕፃን ሴቶች በተለይ ሐረርጌ አካባቢ ፍትህ የማያገኙት በሕክምና እና በትራንስፖርት ገንዘብ እጥረት ነው፡፡ ስለዚህ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንደዚህ ዓይነት ወጪዎችን የማይሸፍን ከሆነ ምን ያህል ውጤታማ ሊሆን ይችላል? በማለት ጠይቀዋል፡፡

<u>አቶ አበራ ኃ/ማርያም - ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር</u>

ድህነት multifaceted አይደለም ወይ? ነፃ የሕግ ድጋፍ የተገልጋዮችን የትራንስፖርት፣ የፍርድ ቤት ክፍያዎችን፣ የሕክምና እና ሥራውን ለማስኬድ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ካልሸፈነ የአገልግሎቱ ሙሉ መሆን እና ፍትህን ከመስጠት አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖ አይፈጥርም? የሚል ጥያቄ አንስተዋል፡፡

<u>አቶ አብዱላዚ ሻፊ - ከአዳማ ልዩ ዞን ፍርድ ቤት</u>

የገንዘብ እጦት ለፍትህ መጓደል መሠረታዊ የሆነ ነገር ነው፡፡ በእኛ ተቋም በኩል ለምሳሌ victim fund አለ ከሠራተኞች የሚሰበሰብ፡፡ ተገልጋይ የDNA ምርመራ ወጭ ሊኖርበት ይችላል ይህን መንግሥት ሊሸፍን ይገባል በማለት መሠረታዊ ለሆኑ ነገሮች ወጭን መሸፈን የነፃ የሕግ አገልግሎት አካል መሆን እንዳለበት አስቀምጠዋል፡፡

<u>አቶ ማንደፍሮ ሶሬቻ - ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ</u>

በየዩኒቨርሲቲው የሚገኙ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ማዕከላት በውጭ በሚገኙ ፍንዶች አማካኝነት የሚደገፉ መሆናቸውን ይታወቃል ፡፡ ሶሻል ፈንድ ማግኘት ከባድ ከመሆኑም በላይ መጠኑም እጅግ አናሳ ነው፡፡ በመሆኑም የመንግሥት አካል ይህን ኃላፊነት ቢወስድ መልክም እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡

<u>አቶ እንዳልካቸው ወርቁ - ከጠቅላይ ዐ/ሕግ</u>



ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት በምን አግባብ የአስተዳደር ጉዳዮችን ሊያካትት እንደሚችል ውይይት አድርጋችኋል ወይ? የሚል ጥያቄ ለቡድን 1 አቀርበዋል፡፡

<u>አቶ ዳዊት በሪሁን - ከሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ</u>

ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡ ማእከላት በሚገባ ማዋቀር ከተቻለ ሁሉንም አገልግሎቶች መስጠት እንደሚቻልና እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

<u>አቶ ዘመኑ የስጋት - ከድሬ ደዋ ዩኒቨርሲቲ (የቡድን 1 ተወካይ የቡድን ውይይቱን አቅራቢ)</u>

ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትን በሚመለከት የተገልጋዮቹን መሠረታዊ ወጭ መሸፈን ቢቻል መልካም እንደሆነ እና ኃላፊነቱንም መንግሥት መውሰድ ቢችል መልካም እንደሆነ ጠቅሶ በዩኒቨርሲቲያቸው ሕጉ ምን ይላል የሚል የሬዲዮ ፕሮግራም ጭምር እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ የበጎ አድራጎት ማኅበራትን አስመለክቶ ገንዘብን ከማግኘት አንፃር ሕጉ ገደብ የሚጥል በመሆኑ ይህን ወጭ መሸፈን ከባድ እንደሚሆን ጨምረው አስረድተዋል፡፡

ቡድን 2 - የአገልግሎቱ ተደራሽነት በሚመለከት (ሶፋኒትመኮንን -ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (የቡድን 2 ተወካይ የቡድን ውይይቱን አቅራቢ))



የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ተደራሽነት ከተለያዩ ማዕዘናት በቡድን ውይይት ወቅት የቃኟቸው ሲሆን የመጀመሪያው የአገልግሎቱ ተደራሽነት በጂኦግራፊያዊ መንገድ የቃኙት መሆኑን ፤ ይህን አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በከተሞች አካባቢ የሚበዙ መሆናቸውን ፤ ወደ ክልልና የገጠር አካባቢዎች እጅግ በጣም ውስን እና አገልግሎቱ አለ ለማለት አስቸጋሪ እንደሆነ የቡድኑ ተወካይ አቅራቢ ከጠቀሙ በኋላ የሚሰጠው አገልግሎቱ በቂና ጥራት ያለው ስለመሆኑ አጠራጣሪ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ከቃል ምክር በፍ/ቤት ቀርቦ እስከ መከራከርና እስከ ማስማማት ድረስ ሊዘልቅ እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

የአገልግሎቱ ጥራትን በተመለከተ የሕግ ድጋፉን የሚሰጡ ባለሙያዎች አቅምና ተጠያቂነት፣ የፋሲሊቲዎች መኖር እንዲሁም በሚይዟቸው ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ክትትል ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመው ለውሳኔ ሰጭ አካላት ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃግብሮች ተቀርፀው ሥልጠናዎች ሊሰጡ እንደሚገባ፤ ውሳኔ ሰጭ ባለድርሻ አካላትም ወጥና ሙሉ የሆነ የሕግ ሥራዓትና የተቋም መዋቅር በመዘርጋት በቂ በጀት በመመደብ፣ በአገልግሎት ሰጭ አካላት መካከል ትብብርና ቅንጅት መፍጠር፣ ሥልጠና እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች መፍጠር ላይ ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባ አስቀምጠዋል፡፡ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ሳይሆን በሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው አካላት ጭምር ሊሰጣቸው እንደሚገባ የግል አቋማቸውን ጭምር ገልፀዋል፡፡

ከላይ የተቀመጡ ሁኔታዎችን ለማሳካት ኃላፊነቶችን በምን አግባብ ማን መውሰድ እንዳለበት በመንግሥት እና መንግሥታዊ ባለሆኑ ተቋማት መካከል የሥራ ድርሻ ክፍፍል በማድረግ በቡድን ውይይት ወቅት የተነሱ ጉዳዮች መሆናቸውን የጠቀሱት አቅራቢው በመንግሥት በኩል ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት፣ ተቋማዊ መዋቅሮችን በመዘርጋት፣ ገለልተኛ የሆነ ተቆጣጣሪ አካል እንዲቋቋም በማድረግ፣ በጀት በመመደብ እና በቂና ጥራት ያለው አገልግሎት የማቅረብ ኃላፊነት እነደለበት አመልክተዋል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትደግሞ ግፊት የማድረግ፣ የገንዘብ ድጋፍ፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች፣ የመተባበር እና ኔትዎርክ የመፍጠርና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

የቀረበው ገለፃ ላይ ጥያቄና አስተያየት

<u>አቶ አበራ ኃ/ማርያም - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር</u>

ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ለግለሰቦች ብቻ ሳይሆን በሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው አካላት ጭምር ሊሰጥ እንደሚገባ ያነሱ መሆኑን አስታውሰው ለእነዚህ corporate bodies ጥብቅና መቆም ወይም ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት luxury አይሆንም ወይ?ምን ያህል reasonable ነው? ሲሉ ጠይቀዋል።

<u>አቶ ዘመኑ የስጋት - ከድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ</u>

በልዩ ሁኔታ ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች አገልግሎቱ መሰጠት እንዳለበት የተገለፀ ሲሆን እነዚህ አካላት ጠበቃ የመቅጠር የገንዘብ አቅም ያላቸውቢሆን እንኳ አገልግሎቱ ሊሰጣቸው ይገባል ወይ?" የሚል ጥያቄ አንስተዋል።

<u>ወ/ሪት ትንቢት ወርቁ - ከዕምባጠባቂ ተቋም</u>

ተደራሽነት ከጥራት አንፃር የተመለከታችሁ መሆኑን የተገለፀ መሆኑን ጠቅሳ ከግንዛቤ ማስጨበጥ አንፃር የተመለከቱ መሆን አለመሆን ላይ ጥያቄያቸውን አንስተዋል።

<u>አቶ ፈቃዱ ደምሴ - ከጠቅላይ ዐ/ሕግ</u>

በኛ ሀገር የመክፈል አቅም ማለት በራሱ ምን ማለት ነው ምንድነው መለኪያው; በማለት የጠየቁ ሲሆን ተጋላጭ የሆነ አቅም ያለው ሰው በምን አግባብ ነው አገልግሎቱን የሚያገኘው? ሲሉ ጥያቄቸውን አክለዋል።

<u>አቶ አብዱላዚ ሻፊ - ከአዳማ ልዩ ዞን ፍርድ ቤት</u>

ነፃ የሕግ ድጋፍ ማዕከላት በከተሞች ቁጥራቸው አያሌ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ጂአግራፊካሊ በገጠራማና ከከተማ ሩቅ አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች አገልግሎቱ ተደራሽ አለመሆኑ እርግጥ እንደሆነ ጠቅሰው ጂአግራፊካሊ እራሱ vulnerable areas የሉም ወይ? በማለት ጠይቀዋል፡፡

<u>ሶፋኒት መኮንን - ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ</u>
<u>(የቡድን 2 ተወካይ የቡድን ውይይቱን አቅራቢ)</u>

ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ለተጎጂዎች በቅጡ ባለድረሰበት ሁኔታ በሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው አካለት አገልግሎቱ ሊቀርብ ይገባል የሚለው luxury ሊመስል የሚችል መሆኑን ጠቅሰው ይህ አቋም የግላቸው እንጂ የቡድን አለመሆኑን አመልክተዋል፡፡አንድ አንድ ኮርፖሬት ቦዲስ እንደሚታሰበው የገንዘብ አቅም ላይኖራቸው ይችላል ወይም ያላቸውን ካፒታል መጠቀም በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ሴቶች በማኅበር ተደራጅተው እንጀራ ጋግረው ለማቅረብ ዓላማ ተቋቋመው ያላቸውን ካፒታል በእንድ ምክንያት መጠቀም ካልቻሉ አገልግሎቱ ለነርሱም ቢሆን ተደራሽ መሆን እንዳለበት አቋማቸውን አንፀባርቀዋል፡፡

ተጋላጭ መሆንና ድሃ መሆን በተናጠል ወይስ በጣምራ ነው የሚታየው? የሚለውን በተመለከተ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች በአብዛኘው ጊዜ ኃብት ቢኖራቸው እንኳ በተለያየ ምክንያት ተጋላጭ የሆኑበት ጉዳይ ኃብታቸውን ጠበቃ ለመቅጠር እንዳይጠቀሙበት ሊያደርጋቸው ስለሚችል ለነዚህ ሰዎች አገልግሎቱ ሊነፈግ እንደማይገባ አስታውቀዋል፡፡

<u>ሙሉቀን ይታይህ - ደ/ብርሃን ዩኒቨርሲቲ</u>

ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች ገንዘብ ካላቸውና ይህን ኃብታቸውን መጠቀም በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ያሉ እንደሆነ የጥብቅና ገበያውን መጠቀም የሚችሉ እንደሆነ ጠቅሰው ነፃ የሕግ ድጋፍን በሚመለከት የግንዛቤ መስጨበጫ ሥራ በሰፊው ሊሰራ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ቡድን 3 - አገልግሎቱ ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን በሚመለከት (አቶ ማንደፍሮ ሶሬቻ - አርሲ ዩኒቨርሲቲ (የቡድን 3 ተወካይ የቡድን ውይይቱን አቅራቢ)





ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው አገልግቱ ወጥ፣ ግልፅነት የተሞላበት፣ ተገልጋዩን በአግባቡ የለየ፣ ተጠያቂነት የሚሰማቸው ባለሙያዎች፣ ወዘተ የሚያሟላ መሆን እንዳለበት አንስተዋል፡፡ ነጻ የሕግ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት እንደየሁኔታው የreferral ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባቸውና networked database system ጭምር እንደሚያስፈልጋቸው ገልፀው ይህ ዓይነት አገልግሎት እንዲኖር የመጀመሪያው ነጥብ የሕግ ማዕቀፍ የሚያስፈልግ መሆኑንና ረቂቅ ሕግ ተዘጋጅቶ፣ በይዘት ደረጃም ስያሜ፣ መግቢያ፣ ትርጉምና ዓላማ፣ ተጠያቂነት፣ የአገልግሎት ሰጭ መብትና ግዴታዎችን እንዲሁም የሪፖርቲንግ ሥርዓትን ያስቀመጠ መሆን እንዳለበት አስቀምጠዋል፡፡

ቡድን 4 - አገልግሎቱ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶችን በሚመለከት (አቶ አሸናፊ ጥላሁን - ከጅማ ዩኒቨርሲቲ (የቡድን 4 ተወካይ የቡድን ውይይቱን አቅራቢ)





ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎቱን ለማግኘት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች መካከል የመጀመሪያው በማህበረሰቡ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ተጋላጭ መሆንን የሚመለከት መሆኑን ጠቅሰው በአብዛኘው ጊዜ በጠበቆችና በሕግ ድጋፍ አገልግሎት ማዕከላት መካከል ተገልጋይን ከመምረጥ አንፃር ግጭቶች በተግባር መኖራቸውን ጠቅሰው ከቀበሌ የሚመጣ የድህነት ማረጋገጭ ሰነድ ሌላኛው መስፈርት እንደሆነ ፤ ይህን ማረጋገጫ ማግኘት በራሱ በቢሮክራሲ ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ ችግር ሊኖርበት እንደሚችል አመልክተዋል፡፡ አያይዘውም ሦስተኛው መስፈርት ድሃ መሆንና ጠበቃ ለመቅጠር አቅም የሌለው ስለመሆኑ በቃለመሃላ ማረጋገጥ ሲሆን ይህም የሀሰት መሃላዎች ሊኖሩ እንደሚችሉም የገለፁት የቡድኑ ተወካይ በዋናነት አገልግሎት ፈላጊው እኛ ልንሰጠው ከምንችለው አገልግሎት ውጭ ፍትህን ሊያገኝ የሚችልበት ሌላ አማራጭ ያለው መሆን አለመሆኑ ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ pro bono service'ን በተመለከተ የሚመለከተው አካል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ሲሆን ቁጥጥር የሚደረገው ደግሞ የግል ጠበቃው ፈቃዱን ለማደስ ሲመጣ በመሆኑ ውጤታማ እንዳልሆነ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም በጠቅላይ ዐ/ሕግ፣ በጠበቆችና በሕግ አገልግሎት ማዕከላቱ ግንኙነት ሊኖር እንደሚገባ ጠቁመው የቅንጅት ማጣት የሥራዎች እና የተቋማት ያለአግባብ መደጋገምን ሊፈጥር የሚችል ስለመሆኑ ስጋታቸውን ገልፀው መደበኛ የሆነ የጋራ መግባባት መፈጠር መቻል አለበት ብለዋል፡፡

<u>ቡድን 5 - የ50 ሠዓት ነፃ የህግ ግዴታን በሚመለከት(አቶ ዳዊት በሪሁን - ከሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ (የቡድን 5 ተወካይ የቡድን ውይይቱን አቅራቢ)</u>







የ50 ሠዓት ነፃ የህግ ድጋፍን በተመለከተ በሕግ ላይ የተቀመጠ የጠበቆች ግዴታ ሲሆን ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት ግን ዘርፈብዙ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ በጉዳይ ወይም ኬዝን መሠረት ያደረገ ክፍፍል ቢደረግ የተሻለ እንደሚሆን፤ ቀላልና ውስብስብ ኬዞችን በመቀላቀል ለጠበቆች ተደልድሎ ቢሰጥ መልካም እንደሆነ፤ የጉዳዮቹን ሂደትም በአግባቡ መከታተል ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ በይግባኝ ጉዳዮች ላይ ዳኛው ባስቀመጠው ነገር እንደሚስማሙ ገልጸው ይግባኝን መከታተል ያለበት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አካባቢ በሚኖር ጠበቃ መያዝ እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ያደረጉት 2 የይግባኝ ጉዳዮችን የሚከታተሉ ጠበቆችን እንደቀጠሩ የጠቀሱት አቅራቢው ለችግሮቹ እንደመፍትሄ የጠቀሱት ነጥብ ሀገራዊ ፖሊሲ መቅረፅ ተገቢ መሆኑንና አንድ ገለልተኛ የበላይ ጠባቂ ተቋም እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡



<u>አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - አወያይ</u>

ነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎትን በሚመለከት ብዙ ነጥቦች የሚነሱ መሆኑን ከቤቱ የተነሱ ጥያቄዎች፣ ሃሳብ አስተያየቶች እንዲሁም በቡድን ውይይት የተነሱና በመድረክ የቀረቡ ጉዳዮች እጅግ በጣም ጥሩና ሊሰሩባቸው የሚገቡ ነጥቦች መሆናቸውን ቀጣይ መድረክም ሊኖር እንደሚችል ጠቁመው ለጠቅላይ ዐ/ህግ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የመሰብሰቢያ አዳራሹን በነፃ በመፍቀድ፣ ሃሳብ ሰጭና ተሳታፊዎችን ጭምር በመመደብ ትብብር ስላደረገ አመስግነው፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ክሊኒካል ኤጁኬሽን ፐብሊክ ኢንተረስት ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ በማድረጉ አመስግነው፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማኅበር ስታፍ ሠራተኞች አውደጥናቱ እንዲካሄድ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ያበረከቱ በመሆኑ እንዲሁም የዓውደጥናቱ ተሳታፊ አካላትም መድረኩ ላይ በመታደም እጅግ ንቁ የሆነ ተሳትፎ በማድረጋቸው ምስጋናቸውን በማቅረብ ለሁሉም አካላት ምስጋና አቅርበው ውይይቱ ከቀኑ 11፡30 ላይ ተጠናቋል።

//